# የወያኔ አለንጋ ዕጅ ባሜሪካ

ይነጋል በላቸው

በ«ሠላም ለሁላችሁም» ጀመርኩ ይህችን አጭር አስተያየት፡፡ የአቶ ዘውገ ፋንታን ሀተታ ብርቱካን አሁን አነበብኩ፡፡ ሀገራችን የገጠማትን ዘርፈ ብዙ ችግር እያሰላሰልኩም ብዙ ተከዝኩ፡፡ የወያኔም ዕጅ ምን ያህል ረጂም እንደሆነ ታሰበኝ፡፡ ለነገሩ በብሂሉ «አለንጋ ጣት» ነበር የሚባለው - ግን ነገርን እንዳደረጉት ነውና «አለንጋ ዕጅ» አልኩና ተነሳሁ፤ ዳሩ ዛሬ ዛሬ ምን ባለበት ቆሞ ያለ ነገር አለና ልጨነቅ? ሁሉም ነገር ሲያውም በአሉታዊ መልኩ እዬተለወጠ አይደል ያለ?

የብርቱካንን ግብዣ በሚመለከት ብዙ ተብሎኣል፤ ከሚገባው በላይ ጦዞኣል ማለትም ይቻላል፡፡ አብዛኛው ሕዝበ ኢትዮጵያ እዚህ ባገር ቤት ውስጥ ይልሰውንና ይቀምሰውን አጥቶ በርሀብና በሰቆቃ እየተገረፈ ባለበት ሁኔታ ከዚህ ታላቅ ሀገራዊ መቅሰፍት አንጻር ሲመዘኑ ሚዛን በማይደፉ ጉዳዮች እንድንንጫጫ የወያኔ የዘወትር መሠሪ ሥልት መሆኑን የምናውቅ እናውቃለን፡፡ የትም የሚኖር ኢትዮጵያዊ የወያኔን «በረከት» ማግኘት እንዳለበት የወያኔው ወያኔያዊው ክታበ ዲያቢሎስ የደነገገው ደንብ መሆኑንም ብዙዎቻችን እንረዳለን፡፡ ለዚህ ወያኔያዊ ተልዕኮ ስኬታማነትም በሃይማኖቱና በፖለቲካው ዘርን በዋነኛነት መሥፈርት ባደረገ የተልዕኮ አስፈጻሚ አባላት ምርጫ መሠረት በተመረጡ ሥውርና ግልጽ የሃይማኖት «አባቶች»ና የፖለቲካ «ሊቀ ሊቃውንት» ያላሰለሠ ጥረት ሥራው 24 ሰዓት ይከናወናል፡፡ የብርቱካን የግብዣ ስረዛም የዚሁ ዓለም አቀፍ የወያኔ ዘመቻ አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ሰውየው ለገሠ እኮ « ማንም አያድናችሁም! ፈረንጅ አያድናችሁ - ተቃዋሚ ተብዬዎች አያድኑዋችሁ . . .» ብሎ ቀድሞ እቅጩን ነግሮናል፡፡ ምን አዲስ ነገር አለ? ያው ነው፡፡ የነበረ፤ ያለና የሚቀጥል፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ተወጥረናል፡፡ የለገሠ ኮከብ የብርሃን ኃይልዋ እንዳይደበዝዝ በሰይጣናዊ ቱማታም ይሁን በሲአይኤና ሳይኖ-ኢትዮጵያ የስለላና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ማገዶ እስካገኘች ድረስ እኛም የእሳት ፍም ወነበልባሉና ወያኔያዊ እቶኑ እንደፈጀን እንኖራለን፡፡ ማንም እንዳያድነን የወቅቱ ጉራማይሌ ታሪካችን ፍርደ ገምድል ፍርዱን ጥሎብናልና፡፡

አለቃ ገ/ሃና አሉት የተባለ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ በጣም ርቦኣቸው ቤታቸው ይመጣሉ፡፡ ሚስት ወ/ሮ ማዘንጊያ ምሣ ያቀርባሉ፤ ምሣው ጎመን ነበር ታዲያን - አሉ ነው መቼም፡፡ አለቃ አልወደዱትም - ያን የጎመን ምሣ፡፡

ጣጥለውት ወደጓኛቸው ቤት ውልቅ ይላሉ - ሳይበሉት:: እዚያ የሄዱት በማለፊያ ወጥ እንጀራ ቀርቦላቸው ከጎመን ምሣ ለመገላገል ነው - ባሳባቸው:: እጓደኛቸው ቤት ደረሱ- ዕጃቸውን ኩታራ አስታጠባቸውና በጉጉት የጠበቁት ምሣ ቀረበ:: የቀረበው ምሣ ግን ያው ጎመን ሆነና አረፈው:: እሳቸውም አሉ አሉ - «በየት ዞረሽ ቀደምሽኝ» - ጎመኒቱን ነው እንዲህ ያሉት:: ለማስታወስ ያህል እንጂ ባገራችን ይትበሃል ያደገ ሰው ይቺን ተረት ከነውስጠዘዋ የማያውቅ የለም::

ወያኔ የትም ብንገባ ዞሮ ይጠብቀናል - እንዳለቃ ገ/ሃና የጎመን ምሣ:: እስካሁን ገና ያላረጋገጥኩት ማረጋገጥም የማይቻለኝ ሲያልና ገነት በሚባሉት ምናባዊ የክፉና የደግ ሰዎች የወዲያኛው ዓለም መኖሪያ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወያኔ ያልገባበትን ቦታ ፈልጎ ማግኘት ይከብዳል ብቻ ሳይሆን አይቻልም ባይ ነኝ:: ቃሉ ነው - «የትም ብትገቡ የማልለቃችሁ ታሪካዊ አጥፊያችሁ ነኝ፤ አልመቻችሁም - አልስማማችሁም፤ አላስማማችሁምም:: ብትተውኝም አልተዋችሁም፤ ብተዋችሁ አባቴ ሊቀ ጥልሚያኮስ 'ልጅነቴን አያስጨርሰኝ '::» የለገሠ ትንቢታዊ ቃል ይህ ነበር - አሁንም ይሄው ነው ፤ በሕይወት እስካለ ድረስም እንዲሁ ይህንኑ ትንቢተ ጋንኤል ተግባራዊ እንዳደረገ ይዘልቃል - ፈጣሪ በድንገት በሚፈጥራቸው ድንቅ ልጆቹ የተለዬ ታሪክ እስኪሠራ ድረስ:: ከዚህ አንጻር የመልካም ትውልድ አብነት የሆነች የአንዲት ዕንቁ ብላቴና በስፖርት ፌስቲቫል ላይ በክብር እንግድነት መጋበዝ ይቅርና ኢትዮጵያዊ ሰውነትህን ይዘህ በየትኛውም የዓለም ክፍል የመኖርም መብት የለህም:: እዩዩም ሲዳላ ነው ጌቶቼና ወንድሞቼ:: ስንንጫጫ ደስ ይላቸዋል፤ ርስ በርስ ስንራኮትና ስንወራከብ የመንፈስ ደስታን ያገኛሉ፤ በሁከት ስንተረማመስ ሃሴት ያደርጋሉ፤ የኛ መታወክ የነሱ የኀልውና መሠረት ነው:: የኛ ሥቃይና እንግልት የነሱ የደስታና የድሎት ምንጭ ነው:: እንዲህ ነበር - እንዲህ እንደሆነም ይቀጥላል::

ስለዚህ «ክርስቶስ ሁለት ባላችሁበት ሦስተኛ እኔ አለሁ» እንዳለው እኛም ሁለት ባለንበት ሦስተኛ ወያኔ አለልን - የባሕርይ አባቱን የዲያቢሎስን ግብር ሊከውን:: እናም በሁለት ሰዎች መሃከል እንደሦስተኛ የተገኘ ወያኔ በ22 የስፖርት ኮሚቴ አባላት መሃል 10 ብቻ መገኘቱ ታላቅ ዕድል ነው ወንድሞቼና እህቶቼ:: እርግጥ ነው የሰይጣንና የወያኔ የአረባብ ዘዴ እንደ ሥነ ሕይወት ትምህርታችን በ«ባይናሪ ፊሽን» መልክ ስለሆነ በቶሎ የመራባት ተፈጥሮኣዊ ባሕርይ አለውና የደገኞቹ ውሳኔ ጥቂት ሳይቆይ በመቀልበሱ ምክንያት ብናዝንም ባልተተገበረው

የግብዣ ውሳኔ ለትንሽ ጊዜ መደሰታችን በራሱ ትልቅ ድል ነው:: ለብርቱዬ ግን በወያኔ የዕጅ አዙር ድግስ ላይ ብትገኝ ባትገኝ ለውጥ የለውም - እንዲያውም ይቅርባት፤ ቀበሮዋ ገደል ላይ ብስል ወይን አይታ ዘልላ ዘልላ ስላልደረሰችባት «አልበሰለችም» ብላ በመተው እንደተጽናናችው አይደለም ነገሬ - በፍጹም :: በኛ ልብ ውስጥ ተንሠራፍታ ለዘላለም ተቀምጣለችና በርሱዋ ሰበብ የማያስፈልግ ወያኔያዊ ህንፍሽፍሽ ውስጥ መግባት አይገባምና ብርቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለታሪክ ብቻ ተዋት፤ አሁን ጥቂት ትረፍበት: የወያኔ ጀሌ አፍ ማሙዋሻም አናድርጋት፤ ለመሾሚያና ለብርጭቆ ማጋጭያም(ቺርስ መባባያ) አንዳርጋት:: ፌስቲቫሉንም ለነሱ ልቀቁላቸው ይንጎማለሉበት:: ይህን ዕድል ነገ ላያገኙት ይችላሉና ባለቻቸው ጊዜ ሲፈልጉ ሼሁን ሲያሻቸው ልደቱን ወይም አንዱን አረጥራጭ ተቃዋሚ ነኝ ባይ ጥቅመኛ ይጋብዙበት:: የኢትዮጵያ ሕዝብ መዥገሮቹን ለመንቀል አቅም ሳይሆን ሁነኛ አመራር የሚሰጠው አጣ እንጂ እነኝ ህ የታሪክ ጎዶች አይጫወቱበትም ነበር:: በፖለቲካውና በንግዱ ዓለም የተሠማሩ መዥገሮች በሕዝብ ደም ወፍረው ስላበጡ የመፍረጫ ጊዜያቸው ደርሶኣል- አንድም በተፈጥሮኣዊ ሂደት በራሳቸው ጊዜ ይፈርጣሉ፤ አንድም ፈጣሪ ባመቸው ጊዜና ባሰኘው ወቅት ሃቀኛ ኢትዮጵያውያንን አስነስቶ ያፈርጣቸዋል:: አሁን ፈጣሪ ለነጻነቱ ፋና አብሪነት ሰው አጥቶ እንደሆነስ እንዴት ይታወቃል? ብዙውን ወገናችንን ስናይ በርግጥም ፈጣሪ ሰው እንዳጣ መገመት እንችላለን:: እዚህ አገር ቤት ውስጥ እኮ ሰው ማግኘት እዬከበደን ነው:: በዚህ ላይ እመለስበት ይሆናል - ሌላ ጊዜ:: « ሁሉም ሌባ ነው ሚደድ፤ ክርስቶስ ወርደህ ፍረድ» የምንልበት ጊዜ ላይ ነው የምንገኘ:: ሆድ አምላኩ በዝቶ ምድር ቃጤ ሆናለች፤ ፈጣሪን ማመለክ÷ ለጎሊና ተገዢ መሆን . . . ፋራነት ከሆነ ሰነበተ:: ሀገሪቱ በማኘኛውም አቅጣጫ ጅብ እያፈራች ያለች ነው የምትመስል:: አሁኑኑ ልጨርሰው ነው እንጄ እመለስበታለሁ ብዬ ሳበቃ?

ያቺን ማጭበርበሪያ ግን ተዋት፤ « የስፖርቱ ተቋም ከፖለቲካ ውጭ . . .» ምናምን የሚባለው ነገር የቁጩ ነው:: ዱሮ አንድ አሁን ደራሲዋን የማላስታውሰው «Everything is Politics» የሚል መጽሐፍ ቃኘት ማድረጌ ይታወሰኛል:: እውነት ነው :: ዝም ብትል ፖለቲካ ነው:: ብትናገርም ፖለቲካ ነው:: ሁሉም ነገር ፖለቲካ ነው:: ከፖለቲካ ውጭ መኖር የሚቻለው መቃብር ውስጥ ብቻ ይመስለኛል:: እሱንም እጠራጠራለሁ:: ማን ያውቃል እዚያስ «ቡና

የሚጠራሩት» በዘርና በጎሣ ፥በጎጥና በሃይማኖት ቢሆንስ? የሚሞተው ሰው እንደሁ ከሁሉም ሃይማኖትና ከሁሉም ዘውግ ነው፤ መጠርጠር አይከፋም ወዳጆቼ! የወያኔ የዘር ፖለቲካ ያልበከለው የአሠራር ዓይነት የለም።

እናስ ወገን - ፊጂንና ጂቡቲን የሚያካክሉ ራሳቸውን የቻሉ ነጻ ሀገሮችን ሊፈጥር የሚችለው ስንትና ስንት የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው ዓለም የተበተነው ለሸርሸርና ቱሪስት መሆን አምሮት ነው? በየቀኑስ በስደት ወደ ውጭ የሚጎርፈው ሕዝብ ሀገሩንና ሥልጣን ላይ ያለውን «ወርቅ መንግሥት» ጠልቶ ነው? «ለምን ይዋሻል?» ማለትስ አሁን ነው። ማህበሩ ከፖለቲካ ውጭ ነው ምን ማለት ነው? ምን ዓይነት ተጨፈኑና እናሞኛችሁ ነው? ቂሎች! ሣር ቅጠሉ ሆዳምና አድርባይ በሆነበት ሠው የጠፋበት ዘመን «የሕዝብ ስደት ይቁም፤ ለማስመሰያነት እንኩዋን በማይበቃው ቁጨ የወያኔ ዴሞክራሲ ሳይሆን ሕዝብ በሚመርጠው እውነተኛ አስተዳደር ሀገር ትተዳደር፤ ከርሀብና ከጭቆና ወጥተን እኛም የሀገር ባለቤትነትና የዜግነታችን ወግ ማዕረግ ይድረሰን፤ . . .» በሚል መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄ ምክንያት የታሠረችና የወጣትነት ለጋ ዕድሜዋን ለሕዝብ ስትል በዬእሥር ቤቱ ለተንከራተተች የሕዝብ ልጅ በአንድ የስፖርት ፌቲቫል ላይ በክብር እንግድነት መገኘት ይነስባት? ጉደኛ የኮሚቴ አባላት ከጉደኛ የስፖርት ቤተሰብ ጋር! እዚህስ የያዘ ይዞን ነው እንዴት ዴሞክራሲ አለ በሚባልበት ታላቅ ምድር የማህበር ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ዝም ይባላል? በዚያ ሀገር ይህችን በአንጻራዊ አነጋገር ኢምንት የሆነች ነጻነት ማስከበር ያልቻለ ወገን ለትልቁ ሀገራዊ ሓርነት እንዴት መታገል ይቻለዋል? ለዚህ ለዚህማ ማሕበሩ ለምን ተመሠረተ? እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ተጎምሮልናል አይደለም እንዴ ስንትና ስንት የወያኔ ማህበር? የስፖርት ማህበሩ ለምን አዲስ አበባ መጥቶ የስፖርት ኮሚሽኑን ቢሮ አይረከብም ታዲያ? ከአባላቱስ ብዙዎቹ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ያገኙት አሁን ጠብ እርግፍ የሚሉለትን ወያኔ በኢዴሞክራሲያዊነት ላማሪካው መንግሥት አሳብቀው አይደል? በአንድ ነባራዊ እውነት እንስማማ - ዛሬ የዚህ መንግሥት ዴሞክራሲያዊነት ድንገት ተከስቶላቸው የሚያደርጉትን ቢያደርጉም ታሪክ ይህንን ድርጊታቸውን መዝግቦ ያስቀምጠዋል፤ ነገ እነሱ ለማፈር ዕድሉን እንኩዋን ባያገኙት የተረገመው የትውልድ ሐረጋቸው ሲያፍርባቸውና ከመቃብራቸው በላይ በጥቁር መዝገብ ሠፍሮ በሚቀመጠው በነሱ ዕኩይ ተግባር ሲሳቀቅባቸው ይኖራል። ከማይረባ ጮማ ግሣት የራስ ያሉት የጎመን ብስናት

**ይሻላል፡፡ ከአንድ እንጀራ በላይ ለማይዝ ሆድ ይህን ያህል ወርዶ በሀገርና በወገን ላይ ወንጀልና ደባ መፈጸም ከይቅርታ በላይ ነው፡፡ መንጋቱ አይቀርም፤ እናም እነዚህን በውጭም ሆነ በውስጥ ያሉ ሆድ አደር ነቀዞች ይነጋል በሉዋቸው፡፡ ከምሥጋና ጋር ጨረስኩ፡፡**

For any constructive comment: yinegal3@gmail.com